50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
Telephone: 1300 650 172
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

Amharic | አማርኛ

ማክሰኞ መጋቢት 11፣ 2025 እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር

**የ33 Alfred St፣ ሰሜን ሜልቦርን ቀጣይ እርምጃዎች አስፈላጊ ዝማኔ**

የዳግም ግንባታውን እያንዳንዱ ደረጃ በወቅታዊነት ለእርስዎ ማድረስ እንፈልጋለን። ይህ ደብዳቤ ስለሚከተሉት መረጃ አካተዋል፡-

- በሰሜን ሜልቦርን ተጨማሪ እና የተሻሉ ቤቶችን የመገንባት እቅዳችን
- የእኛ ሠራተኞች የት ማግኘት እንደሚቻል
- ስለ ዳግም ግንባታው ተጨማሪ ለማወቅ የት መሄድ እንደሚቻል

**የረመዳን ጾም መጾም**

- በአሁን ወቅት በማህበረሰባችን ውስጥ ብዙሃኑ የረመዳን ጾም ላይ መሆናቸውን እንረዳለን እና እናከብራለን።
- ስለእነዚህ ቀጣይ እርምጃዎች የማህበረሰብ መረጃ ክፍለ ጊዜዎች ሚያዝያ ውስጥ (ከረመዳን በኋላ) እናካሂዳለን።
- የእነዚህ ክፍለ ጊዜዎችን ቀናት እና ሰዓታት የያዙ ልጥፎች በእርስዎ ህንጻ መግቢያ ላይ ይደረጋሉ።
- ከዚያ በፊት እኛን ማነጋገር ከፈልጉ፣ የእኛ ሠራተኞች ሃሙስ መጋቢት 13፣ ከጠዋት 9:00 - ምሽት 5:00 እንደ አውረፓውያን አቆጣጠር በሰሜን ሜልቦርን የመኖሪያ ቤቶች ቢሮ ይገኛሉ።

**በእርስዎ ቋንቋ የተተረጎመውን መረጃ ለማግኘት ይቃኙ**

**በታሕሳስ ሃሳባቸውን ላጋሩ ሁሉ እናመሰግናለን**

እንደ የታሕሳስ የማህበረሰብ ተሳትፎ አካል ለ33 ጎዳና ኣልፍረድ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምላሻቸውን እና ሃሳባቸውን ለሰጡን ሁሉ እናመሰግናለን።

የእርስዎ ግብረ መልስ ለአዳዲስ ህንጻዎች እና የማህበረሰብ ቦታዎች ንድፎችን ይጠቁማል።

- በወደፊት ቤቶች፣ ህንጻዎች፣ የማህበረሰብ ቦታዎች እና ሰፈሮች ለእነሱ ምን አስፈላጊ እንደሆነ ከ165 ተከራዮች ሰምተናል።

- ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ በሚገባ የተነደፉ እና በማህበረሰብ ላይ ያተኮሩ አዳዲስ ህንጻዎች እና የውጪ ስፍራዎችን በመገንባት አስፈላጊነት ላይ የሰጡትን ግብረ መልስ ሰምተናል።
- እንዲሁም የተለያየ መጠን ላላቸው ቤተሰቦች መኖሪያ ቤት ስለማቅረብ አስፈላጊነት ሰምተናል።

**አሁን ለዚህ ዳግመ ግንባታ የሚሆን እቅድ የሚያስገባ የፕሮጀክት አጋር እየፈለግን ነው**

በ33 ጎዳና ኣልፍረድ፣ ሰሜን ሜልቦርን 300 የማህበራዊ ቤቶችን ጨምሮ ቢያንስ 800 አዲስ ቤቶችን ለመገንባት እ ና ለማስተዳደር ንድፈ ሀሳብ የሚያቀርብ የፕሮጀክት አጋር እየፈለግን ነው። ሁሉም መሬት በሕዝብ ባለቤትነት ስር ይ ቆያል።



*በአቦትስፎርድ ጎዳና ፣ ሰሜን ሜልቦርን (Abbotsford St North Melbourne) የተገነቡ አዳዲስ ኃይል ቆጣቢ ቤቶች በ2025 ተከፍተዋል።*

አጋሩ የማህበራዊ፣ ተመጣጣኝ እና የገበያ ኪ ራይ ቤቶችን የመገንባት እና የማስተዳደር ል ምድ ይኖረዋል።

እያንዳንዱ ንድፈ ሀሳብ ባለው ጥቅም መሰረ ት በጥብቅ የግምገማ ሂደት ይገመግማል

ከፕሮጀክት አጋር ጋር በመስራት በVictoria ለሚኖሩ ተጨማር ሰዎች፣ ለት/ቤቶች፣ አገልግ ሎቶች እና ትራንስፖርት ቅርብ የሆኑ ይበልጥ ዘመናዊ፣ በሚገባ የተነደፉ እና ኃይል ቆጣቢ ቤቶችን ማቅረብ እንችላለን - ልክ በአቦትስፎ ርድ ጎዳና በቅርቡ እንደተጠናቀቁት አዳዲስ ቤ ቶች (በሥዕሉ ላይ ያለው)።

**የእርስዎን ሃሳብ ለማቅረብ ተጨማሪ እድሎች**

የአዳዲስ ቤቶች፣ ህንጻዎች እና የማህበረሰብ ቦታዎችን ንድፎች ለማዘጋጀት ከፕሮጀክት አጋር ጋር ስንሰራ፣ ንድፎችን ለማየት እና ግብረ መልስ ለመስጠት ተጨማሪ እድሎች ይኖርዎታል።

**የእኛን ቡድን የት ማግኘት እንደሚቻል**

ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም የእኛን ቡድን ማነጋገር ከፈለጉ፣ ሠራተኞች ሃሙስ መጋቢት 13፣ ከጠዋት 9:00 - ምሽት 5:00 እንደ አውረፓውያን አቆጣጠር በሰሜን ሜልቦርን የመኖሪያ ቤቶች ቢሮ ይገኛሉ።

**ወቅታዊ መረጃ ያግኙ**

ይሄን ይጎብኙ፦ https://bighousingbuild.homes.vic.gov.au/precincts/north-melbourne-precinct በቋንቋዎ የሚገኙ ግብዓቶችን ጨምሮ ለመረጃ እና ዝማኔዎች።